Cumbria, Northumberland, Tyne and Wear
NHS Foundation Trust

# ለህክምና ወደ ሆስፒታል መግባት

(የአእምሮ ጤንነት ህግ ክፍል 3 1983)

| | |
|---|---|
| 1. የህመምተኛው ስም | y |
| 2. የእርስዎ እንክብካቤ ኃላፊነት ያለው ሰው ስም (የእርስዎ "ኃላፊነት ያለበት ሀኪም") ክሊኒክ | |
| 3. የሆስፒታሉ እና የክፍሉ ስም | |
| 4. በ ህግ ክፍል 3 ስር እስሩ የተጀመረበት ቀን | |

## ለምንድን ነው ሆስፒታል ውስጥ ያለሁት?

እዝህ ሆስፒታል እንዲቆዩ የተደረጉት በ1993ቱ የአእምሮ ጤንነት ህግ በክፍል 3 መሰረት ነው።

ይህ ማለት ሁለት ዶክተሮች የአእምሮ ችግር አለብዎ ብለው ያስባሉ እናም ህክምና እና እንክብካቤ እንዲያገኙ ወደ ሆስፒታል ውስጥ መሆን አለብዎት ፡፡

## እዚህ ምን ያህል ጊዜ እቆያለሁ?

የሚፈልጉትን ሕክምና እንዲሰጥዎ በመጀመሪያ እስከ ስድስት ወር ሊቆዩ ይችላሉ ፡፡ የእንክብካቤዎ ኃላፊ የሆነው ሰው (በእርሰዎ ኃላፊነት ያለበት ሀኪም) እርስዎ መሄድ አለብዎት ብሎ ካልወሰነ በስተቀር በዚህ ጊዜ መውጣት የለብዎትም ፡፡ ለመውጣት ከሞከሩ ሰራተኞቹ ሊያስቆሙዎት ይችላሉ ፣ ከወጡ ደግሞ ተገደው ሊመለሱ ይችላሉ ።

## ከዝያስ ምን ይሆናል?

ከሆስፒታል ለመውጣት ብቁ ነዎት ብለው ሲያስቡ ኃላፊነት ያለው ሐኪምዎ ይነግርዎታል። ኃላፊነት ያለው ሃክምዎ ከስድስት ወር በላይ ሆስፒታል ውስጥ መቆየት አለብዎ ብለው ካሰቡ እስከ ስድስት ወር ድረስ በሆስፒታል ውስጥ የሚቆዩትን ጊዜ እና ከዚያ በኋል ለሌላ ስድስት ወር ይታደስና እስከ አንድ ዓመት ጊዘው ድረስ ይቆያሉ ። በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ስለዚህ ጉዳይዎ ሃኪምዎ ያነጋግርዎታል።

## ምን አይነት ህክምና ነው የሚሰጠኝ?

ኃላፊነት ያለው ሃኪምዎ እና ሌሎች የሰራተኞች አባሎች እርስዎ ያስፈልጎታል ብለው ያሰቡትን ሕክምናዎች ሁሉ ይነግርዎታል ። በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ምክሮቻቸውን መቀበል ይኖርብዎታል።

ከሶስት ወር በኋላ፣ ለአእምሮ ህመምዎ ስለሚሰጥዎ ማንኛውም መድሃኒቶች ልዩ ህጎች አሉ ። መድኃኒቶችን የማይፈልጉ ከሆነ ፣ ወይም እርስዎ ይፈልጉ እንደሆነ ለመናገር በጣም ከታመሙና ካልቻሉ ከዚህ ሆስፒታል ያልሆነ ዶክተር ሊጎበኘዎት ይችላል ። ይህ ገለልተኛ ሐኪም እርስዎን እና እርስዎን ከሚያውቋቸው የሆስፒታል ሰራተኞች ጋር ይነጋገራል ። ገለልተኛው ሀኪም ምን ዓይነት መድሃኒት እና ህክምና እንደሚሰጥዎ ይወስናል ። ድንገተኛ ካልሆነ በስተቀር ያለእርስዎ ስምምነት ሊሰጡ የሚችሉት ብቸኛ መድኃኒቶች እነዝህ ብቻ ናቸው ።

ይህ ገለልተኛ ሐኪም SOAD (ለሁለተኛው አስተያየት የተሰየመ ዶክተር) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የአእምሮ ጤና ሕግ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል በሚቆጣጠር ገለልተኛ ኮሚሽን ይሾማል።

ለአንዳንድ ልዩ ህክምናዎች እንደ ኤሌክትሮኮንቫልሲቭ ቴራፒ (ECT) ለመሳሰሉት የተለያዩ ህጎች አሉ። ሰራተኞቹ ከእነዚህ ልዩ ህክምናዎች ውስጥ አንዱን ያስፈልጎታል ብለው ካመኑ ደንቡ ይብራራሎትና ሌላ በራሪ ወረቀት ይሰጥዎታል

## ይግባኝ ማቅረብ እችላለሁ?

አዎ፣ በክፍል 3 ስር ሆስፒታል ለማቆየት በሚወስነው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላሉ ።

ይህንን ለማድረግ የሆስፒታል አስተዳዳሪዎች እንዲለቁዎት መጠየቅ ይችላሉ ። ይህንን በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ይችላሉ ። የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጆች ሰዎች በሆስፒታል ውስጥ መቆየት እንዳለባቸው ወም እንደሌለባቸው የሚወስኑ በሆስፒታሉ ውስጥ የተቋቋሙ ልዩ ኮሚቴዎች ናቸው ። ለቀው እንዲወጡ ውይም እንዳወጡ ከመወሰናቸው በፊት ሊያነጋግሩዎት ይፈልጉ ይሆናል ።

በአካባቢዎ ለሚገኘው የአእምሮ ጤና ህግ ቢሮ የሆስፒታል አስተዳዳሪዎች መጻፍ ይችላሉ ወይም፣

| | |
|---|---|
| Mental Health Act Office St Nicholas Hospital Jubilee Road<br>Gosforth<br>Newcastle upon Tyne NE3 3XT | Mental Health Act Office<br>Carleton Clinic<br>Cumwhinton Drive<br>Carlisle<br>Cumbria<br>CA1 3SX |

ወይም የሆስፒታል አስተዳዳሪዎችን ለማነጋገር የሰራተኛውን አባል መጠየቅ ይችላሉ ::

የቅርብ ዘመድዎ ለሆስፒታል አስተዳዳሪዎች ከሆስፒታል እንዲወጡ ሊፈቅድልዎ እንደሚፈልግ በመናገር ደብዳቤ መጻፍ ይችላል :: ይህ በራሪ ወረቀት ይህ የቅርብ ዘመድዎ ማን መሆን እንዳለበት በበለጠ ያብራራል :: የቅርብ ዘመድዎ ይህን ካደረገ የሆስፒታል አስተዳዳሪዎች በኃላፊነት የተመደበ ሀኪምዎ ለራስዎም ሆነ ለሌሎች ሰዎች አደጋ ሊፈጥሩ ይችላሉ ካላለ በ 72 ሰዓታት ውስጥ ይወጣሉ  :: ይህ ከተከሰተ፣ የቅርብ ዘመድዎ አሁንም መልቀቅ እንደሚፈልጉ ለሆስፒታሉ አስተዳዳሪዎች እንደገና ከመጠየቅዎ በፊት ሌላ ስድስት ወር ይሆናል እስከዚያ ጊዜ በሆስፒታል ውስጥ የቆዩ ከሆነ ::

እንዲሁም ከእንግዲህ በሆስፒታል ውስጥ መቆየት እንደለለብዎት በልዩ ፍርድ ቤት በኩል መጠየቅ ይችላሉ ::

## ልዩ ፍርድ ቤት ምንድን ነው እናም ምን ይፈጥራል?

ልዩ ፍርድ ቤቱ ከሆስፒታል ለቀው ለመሄድ  ይፈቀድልዎታል ወይም አይፈቀድልዎትም የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ገለልተኛ ፍርድ  ቤት ነው። ከእርስዎ እና እርስዎን ከሚያውቁ የሆስፒታሉ ሰራተኞች ጋር ስብሰባ ያደርጋል :: ይህ ስብሰባ “ችሎት” ይባላል :: ከፈለጉ ሌላ ሰው ወደ ችሎቱ እንዲመጣና እንዲረዳዎ መጠየቅ ይችላሉ:: ከችሎቱ በፊት፣ የልዩ ፍርድ ቤቱ አባላት ስለ እርስዎ እና ስለ እንክብካቤዎን አስመልክቶ ከሆስፒታሉ የተገኙ ሪፖርቶችን ያነባሉ :: ከልዩ ፍርድ ቤቱ አባላት አንዱ እርስዎን ለማነጋገር ይመጣል ::

## ለልዩ ፍርድ ቤቱ የማመለክተው መቼ ነው?

በክፍል 3 ህግ መሰረት በሆስፒታል እንዲቆዩ ለማድረግ ለልዩ ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ ። ከዚያም በኋላ በየሁለቱም ስድስት ወራት አንድ ጊዜ ማመልከት ይችላሉ ። እና ከዚያ በኋላ በየዓመቱ አንድ ጊዜ በሆስፒታል ውስጥ እንዲቆዩ ይደረጋል።

የቅርብ ዘመድዎ ለሆስፒታል አስተዳዳሪዎች ከሆስፒታል እንዲወጡ እንዲፈቀድልዎት ቢጠይቅና ሃላፊው ሐኪም ግን እርስዎ እንዲለቀቁ አልተፈቀደልዎትም ካለዎት የቅርብ ዘመድዎ ለልዩ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል ። ኃላፊነት ያለው ሃኪምዎ ከሆስፒታል ለቀው መውጣት አይፈቀድልዎትም ብሎ ከወሰነ በ 28 ቀናት ውስጥ የቅርብ ዘመድዎ ይህንን ማድረግ አለበት ።

ለልዩ ፍርድ ቤት ለማመልከት ከፈለጉ በዚሁ መጻፍ ይችላሉ፣

The Tribunals Service (የልዩ ፍርድ ቤት አገልግሎት)
PO BOX 8793
5th Floor
Leicester
LE1 8BN
Tel. 0300 123 2201

ጠበቃ በችሎት እንዲረዳዎ ለልዩ ፍርድ ቤት እንዲጽፍልዎት መጠየቅ ይችላሉ። ሆስፒታሉና የሕግ ማኅበረሰቡ በዚህ ረገድ ልዩ የሆኑ የጠበቃዝርዝር አላቸው ። ለዚህ የጠበቃእርዳታ መክፈል የለብዎትም ። በ ህጋዊ ድጋፍ መርሃግብር መሠረት ከክፍያ ነጻ ነው።

## እርዳታ ከገለልተኛ የአእምሮ ጤና ጠበቃ

ከፈለጉ ከገለልተኛ የአእምሮ ጤና ጠበቃ የመረዳት መብት አለዎት ። እነዚህ ጠበቆች በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ ከሚሳተፉ ሰዎች ነፃ ናቸው ። ስለ ሕክምናዎ እና እንክብካቤዎ ፣ ለምን በሆስፒታል ውስጥ እንደሚቆዩ ፣ ምን ማለት እንደሆነ እና መብቶችዎ ምን እንደሆኑ መረጃ እንዲያገኙ ሊረዱዎት ይችላሉ ። እነሱ እርስዎን ሊያዩዎት ይመጣሉ እናም እርስዎ በእንክብካቤዎ እና በሕክምናዎ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች ምን እንደሚሉዎት ለመረዳት እንዲችሉ ይረዱዎታል ። ከፈለጉ እነዚህን ሰዎች ለማነጋገር ሊረዱዎት ይችላሉ ወይም እነሱ ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ ። በልዩ ፍርድ ቤትም ሊረዱዎት ይችላሉ።

ገለልተኛ የአእምሮ ጤና ጠበቃ አገልግሎትን እራስዎ መገናኘት ይችላሉ ፡፡ እባክዎ የስልክ ቁጥሩን ለማግኘት የሰራተኛውን አባል ይጠይቁ ፡፡ በግል ሊያናግሩ የሚችሉበት ስልክ ሊኖር ይገባል ፡፡ የት እንዳለ የሰራተኛውን አባል መጠየቅ ይችላሉ ፡፡

የጠበቃ አገልግሎቱን እራስዎ ማነጋገር የማይፈልጉ ከሆኑ የሰራተኞችን አባል አገልግሎት እንዲያነጋግሩ መጠየቅ ይችላሉ ፡፡ እንዲሁም የእርስዎ የቅርብ ዘመድ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላል ፡፡

## የቅርብ ዘመድዎን ማሳወቅ

የዚህ በራሪ ወረቀት ቅጅ የአእምሮ ጤና ሕግ መሠረት የቅርብ ዘመድ ነው ለሚባለው ሰው ይሰጣል ፡፡

በአእምሮ ጤና ሕግ መሰረት እንደ ዘመድዎ የሚስተናገዱ የሰዎች ዝርዝር አለ ፡፡ በተለምዶ በዚያ ዝርዝር ውስጥ ከፍተኛው ሰው የቅርብ ዘመድዎ ነው ፡፡ የሆስፒታሉ ሠራተኞች ይህንን ከእንክብካቤዎ እና ሕክምናዎ ጋር በተያያዘ የቅርብ ዘመድዎ ምን መብት እንዳለው የሚያብራራ በራሪ ወረቀት ሊሰጥዎት ይችላል ፡፡

በእርስዎ ጉዳይ፣ እንደተነገረን ከሆነ የርስዎ የቅርብ ዘመድ፣

| |
|---|
| |

የበራሪ ወረቀቱን ቅጂ ይህ ሰው እንዲቀበል ካልፈለጉ፣ ለእርሰዎ ነርስ ወይም ለአንዱ ሰራተኛ ይንገሩ።

## የቅርብ ዘመድዎን መቀየር

ይህ ሰው የቅርብ ዘመድ ለመሆን ተስማሚ ነው ብለው ካላሰቡ ሌላ ሰው በአቅራቢያዎ የሚገኝ የቅርብ ዘመድ ሆኖ እንዲቆይ ለካውንቲው(ወረዳው) ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ ፡፡ የሆስፒታሉ ሠራተኞች ይህንን የሚያብራራ በራሪ ወረቀት ሊሰጡዎት ይችላሉ ፡፡

## የእርሰዎ ደብዳቤ

በሆስፒታል እያሉ ለእርስዎ የሚላኩዎት ሁሉም ደብዳቤዎች ይሰጡዎታል ፡፡ ከርስዎ ደብዳቤ ለመቀበል እንደማይፈልግ ከሚናገር ሰው በስተቀር ደብዳቤዎችን መላክ ይችላሉ ፡፡ ደብዳቤዎች ለእነዚህ ሰዎች እንዳይሄድ ሠራተኞቹ ማስቀም ይችላሉ።

## የአሠራር ደንብ

ለሆስፒታሉ ውስጥ ላሉት ሠራተኞች ምክር የአእምሮ ጤና ሕግ እና የአእምሮ ህመም ላለባቸው ሰዎች ሕክምና መስጠት የሚረዳ የአሠራር ደንብ አለ። ሠራተኞች ስለ እርስዎ እንክብካቤ በሚወስኑበት ጊዜ ደንቡ ምን እንደሚል ማሰብ አለባቸው ፡፡ ከፈለጉ የኮዱን ኮፒ እንዲያዩ መጠየቅ ይችላሉ ፡፡

## ስለአገልግሎቱ፣ አስተያየት፣ሃሳብ፣ ምስጋና ወይም ቅሬታ ቢኖረኝስ?

አስተያየት ሃሳብ ፣ ምስጋና ወይም ቅሬታ መስጠት ከፈለጉ፤

- እርሰዎን በመንከባከብ ውስጥ በቀጥታ የሚሳተፉ ሰዎችን ያነጋግሩ
- ግብረመልስ ቅጽ ለማግኘት የሰራተኛ አባልን ይጠይቁ ፣ወይም በTrust ድህረ ገጽ ላይ www.cntw.nhs.uk (‘ያግኙን ታብ ጠቅ ያድርጉ’ )
- ለቅሬታ ማቅረቢያ ክፍል በስልክ ቁጥር 0191 245 6672 ይደውሉ
- በኢሜል በኩል complaints@cntw.nhs.uk በኩል የሚላከው መረጃ በራስዎ ሃላፍነት የሚላክ መሆኑን ልብ ይበሉ
- አገልግሎቶችን ለማሻሻል ሁል ጊዜ እየጣርን ነው ፡፡ የእርስዎ ግብረ መልስ የእኛን አገልግሎቶች ጥራት ለመከታተል ያስችለናል እና እና ወደ እኛ ያቀረብዎትን ትኩረቶች ጉዳዮች ላይ እርምጃ ይውሰዱ ፡፡

- ግብረ መልስ በሚከተሉት መንገዶች ማቅረብ ይችላሉ፡

- ይህንን ለማድረግ ፈጣኑ መንገድ በአጭሩ የመስመር የዳሰሳ ጥናትበ www.cntw.nhs.uk/poy መሙላት ነው።የየዳሰሳ ጥናትን በእይታዎ መሰርት ይሙሉ፣ በዋርዱ አከባቢ ፣ ከእንግዳ ማስተናገጃ ወይም ከሠራተኞቹ ማግኘት ይችላሉ ።

የሆስፒታሉ ቅሬታ ማቅረቢያ ሂደት ሊረዳዎት ይችላል ብለው ካላመኑ ለነፃ ኮሚሽን ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ ፡፡ ይህ የእንክብካቤ ጥራት ኮሚሽን ተብሎ ይጠራል እናም የአእምሮ ጤና ሕግ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ፣ በትክክል መጠቀሙን እና ህመምተኞች ሆስፒታል በሚቆዩበት ጊዜ በአግባቡ እንደሚንከባከቡ ይከታተላል።
ኮምሽኑን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስረዳ በራሪ ወረቀትየሆስፒታሉ ሠራተኛ ሊሰጥዎ ይችላል።

## ተጨማሪ እርዳታና መረጃ

ስለ ሕክምናዎ እና እንክብካቤዎ የማይረዱዎት ነገር ካለ ፣ የሰራተኛ አባል ሊረዳዎ ይሞክራል ፡፡ በዚህ በራሪ ጽሑፍ ውስጥ እርስዎ የማይረዱት ማንኛውም ነገር ካለ ወይም በራሪ ወረቀቱ ያልመለሳቸው ሌሎች ጥያቄዎች ካሉ እባክዎን የሰራተኛውን አባል እንዲያብራራ ይጠይቁ ፡፡

ለሌላ ሰው የዚህን በራሪ ጽሑፍ ሌላ ግልባጭ ከፈለጉ እባክዎን ይጠይቁ።

Quality Approved Resource

ስለነዚህ ይዘቶች ፣ የማጣቀሻ ምንጮች ወይም የዚህ በራሪ ጽሑፍ ተጨማሪ መረጃ ከታካሚው የመረጃ ማእከል ማግኘት ይችላሉ ፡፡ ስለነዚህ በራሪ ወረቀት ምን እንደሚያስቡ ሊነግሩን ከፈለጉ እባክዎን ያግኙን ፡፡

ይህ መረጃ በጥያቄዎች በበርካታ ቅርፀቶች (ለምሳሌ የአይነ ስውራን ፅሁፍ ፣ በድምጽ ፣ በትላልቅ እትሞች ፣ በቀላል ንባብ ፣ BSL ወይም በሌሎች ቋንቋዎች)በጠየቁት መሰረት ሊቀርብ ይችላል። እባክዎን የታካሚ መረጃ ማእከልን በስልክ ቁጥር 0191 246 7288 ያነጋግሩ

በህሙማን መረጃ ማእከል የታተመ

2020 የቅጂ መብት, Cumbria, Northumberland, Tyne እና Wear NHS Foundation Trust

Ref, PIC/191/0220 February 2020 V9

www.cntw.nhs.uk Tel: 0191 246 7288

የሚገመገምበት ቀን 2021

@cntwnhs CNTWNHS